1.5 የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስልጣን

ሰ/መ/ቁ.145128፡-ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስራቸውን የሚያከናውኑት በሸሪዓ ህግ እና በሀገሪቱ የፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ህግ መሰረት ስለመሆኑ የሐረሪ ክልልን ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 /እንደተሻሻለ/ በአንቀጽ 28 ስር ተመልክቷል። ይህ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የማረም ስልጣን የሚኖረው በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶቹ የጣሱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ጥሰቱም መሰረታዊ የህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ነው።

ሃይማኖታዊ ህጉን መሰረት በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ ሰበር ችሎት ጉዳዩን ሊመረምር የሚችልበት አግባብ አይኖርም። ሸሪዓ ፍርድ ቤት በተከራካሪዉ የቀረበውን የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ይደረግልን ጥያቄ በማለፍ ከሳሽ በጋብቻ የተወለዱ መሆናቸውን በማስረጃ አጣርቶ በሃይማኖቱ ህግ መሰረት የልጅነት እና የወራሽነት ውሳኔ መስጠቱም ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ ጥሰት ፈጽሟል የሚያሰኝ አይደለም። ቅጽ/23

ሰ/መ/ቁ138340፡-በአዋጅ ቁጥር 53/94 በአንቀፅ 6(1) ስር እንደተደነገገዉ አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃድ የሰጠ መሆኑም ሊረጋገጥ ይገባል። በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 53/1994 አግባብ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))፣ 80(3(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 53/94 እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 ጣምራ ንባብ መሰረት ስነ ስርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳላቸው ግንዛቤ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን መመርመር እንጂ ከዚህ ውጪ መደበኛ ሕጎችን መሰረት አድርገው በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊመረምሩ የሚችሉበት አግባብ የለም።

እንዲሁም ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ የደረሰበት መደምደሚያ በሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመዘንበት አግባብ የሌለ መሆኑን በኢ.ፌዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 53/94 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። በመሆኑም በእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች አንጸር

ሲታይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክሩን ሲመሩ በስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ምክንያት ከሌለ ጉዳዩ በፍደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎት ሊታይ አይገባም :: ቅጽ/22

ሰ/መ/ቁ 58119፡-በበታች የሸሪዓ ፍርድ ቤት ባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄያቸውን በመደበኛው ፍርድ ቤት እንዲያስወስኑ በማለት የወሰነውን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ባል ያለው ንብረት አንድ ሻንጣ ልብስ ብቻ ነው በሚል ከሻረው ባል በመጀመሪያ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ብቻ በመንጠልጠል መልስ ቢሰጥ እና በከፍተኛው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የተወሰነበትን አንስቶ ካልተከራከረ በፍ/ቦ/ስ/ስ/ህ ቁጥር 234 (መ) እና 235 መሰረት በግልጽ በክርክር ያልተካደ ነጥብ ስለሚሆን እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ እና ቀድሞ በህግ እውቅና ባለው ከፍተኛ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ባል ቅሬታ ካለው በዚያው ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተዋቅሮ መሰረት ቅሬታውን ለሚመለከተው ይግባኝ ወይም ቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቅረብ ይገባዋል እንጂ እንደ አዲስ ጉዳይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 መሰረት ተቀባይነት ያለው አይደለም:: በመሆኑም ባል በበታች የሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ክስ ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ንብረት እንዳለው ተወስኖ እንዲካፈል እና መደበኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ሚስት በሌለችበት አይቶ ንብረት እንዲካፈል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ቢያጸናው የንብረት ክፍፍል ጥያቄያቸውን በመደበኛው ፍርድ ቤት እንዲያስወስኑ በማለት የወሰነው የመጀመሪያ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ ባል ያለው ንብረት አንድ ሻንጣ ልብስ ብቻ ነው በሚል በከፍተኛው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለተሻረ እና ንብረት የሌለው መሆኑ በከፍትኛው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ ስለተወሰነ ጉዳዩ በህግ አግባብ ስልጣን ባለው አካል አስቀድሞ ስለተወሰነ ይህ ውሳኔ ስላልተሻረ ባል የንብረት ክፍፍል ጥያቄያውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት እንደ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም:: ቅጽ/13

ሰ/መ/ቁ 36677፡-የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወል የዳኝነት ስልጣን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 በአንቀጽ 4 ተደንግጓል:: በዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረት በፌደራል በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው፡-

-በማንናቸውም የጋብቻና የፍች፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያላደረሱ ህፃናት ሞግዚትነት እና የቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ጥያቄ ያስከተለው ጋብቻ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት አቅደው እንደሆነ፤

- የእውቅና ስጦታ /ሂባ/፣ ውርስ ወይም ኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሹ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዥ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፤

- ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ክሶችን ኪሣራ የሚመለከት ሲሆን እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት እንችላለን::

ከዚህ ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የኅሊና ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ክርክር የመሰማትና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የላቸውም። በተከራካሪዎች የተነሳው ጉዳይ የአንደ ሰው ወራሾች በመሆናቸው ምክንያት የቀረበ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ሳይሆን የይዞታ ክርክር ጉዳይ ከሆነ ዐቃው የማን ይዞታ ነው የሚለውን ጉዳይ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት መደበኛ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ናቸው። ቅጽ/3

ሰ/መ/ቁ 72420፡-የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ሳሰማየት በአንድም በሌላም ምክንያት ሬጅደሻች ባይሆኑ መደበኛ ፍ/ቤቶች የዜጐችን ፍትህ የማግኘት መብት ሰማክበር ሲባል ጉዳዩን ማየት አለባቸው። ምክንያቱም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አልመሰከትም ካሉ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማያስተናግዱ ከሆነ ዜጐች ያላቸውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጠብ ነው። የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የፍቸውን ውሳኔ ሰጥተው ንብረት ባያከፋፍሉ መደበኛ ፍ/ቤቶች ንብረቱን ማከፋፈል መቻል አለባቸው። ቅዕ/13

ሰ/መ/ቁ 85873፡-በሸሪዓ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብት ምንጩ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 34(5) ሲሆን የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት ተደራጅተዋል። በአዋጁ የክርክሩን የአመራር ስርዓት ካልሆነ በቀር የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በሸሪዓዊ ስልጣናቸው ስር የሆኑ ጉዳዮችን አቤቱታና ክርክር የሚወሰኑት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ክሰ ወይም አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ባለጉዳዩ ፍቃድ የሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ይገባል። አንድ እርቅ በፍርድ ቤት ሊጸድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልጸው ይኸው ስምምነታቸው ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እርቁ ወይም ስምምነቱ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ክርክሩ እንዲቆምላቸው ሲያመለክቱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ ቁጥር 277 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል። ከዚህ ውጪ, ከፍርድ ቤት ውጪ, በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መስረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው አልባት ያገኙ ሰዎች እርቁ ወይም ግልግሉ እንደተፈረደ ፍርድ ሊቆጠርላቸው የሚገባ እና ውጤቱም በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማጽደቅ ሳያስፈልገው ራሱን ችሎ ሊፈጽም የሚችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 3312 እና 3324 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው። በመሆኑም በውጪ, ሀገር በኢትዮጲያ ቆንስላ ጽ/ቤት ተደረገ የተባለን የፍችና የልጅ አስተዳደግ ስምምነት እንዲጸድቅ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ማቅረብ በህጉ ያልተቀመጠ ስርዓትና በአዋጅ 188/92 አግባብ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ያልተሰጠ ስልጣን ነው። ቅጽ/15

ሰ/መ/ቁ93779፡-ተጋቢዎች ፍቺን አስመልክተው ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦና ክርክር ተካሂዶ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ በሌላ ጊዜ ቡተመሳሳይ ጉዳይ ሀይማኖታዊ ስርዓትን በመጠቀም በሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የፍች ክርክር ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 እና ህገ-መንግስቱ አንቀጽ 34 እንዲሁም ከሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 188/92 አንጻር ተቀባይነት የሌለው ነው። ቅጽ/15

ሰ/መ/ቁ. 45806፡-የፌደራል የመጀመሪያ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ያቀረበውንና የሸሪዓ ፍርድ ቤት መሠረታዊ ሞጣጥ አድርጎ ይዞ በማጣራት ላይ የነበረውን ጉዳይ በተመጣጣይ ጊዜ ውስጥ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን የሚቀርብ ጥያቄ የህገ

መንግስቱን አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 እና የፍትሃብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 8 ንዑስ አንቀጽ 1 "ን" የሚጥስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሚችን ጉዳዜ በጭብጥነት ይዘው በማጣራት ላይ እያሉ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀድሞ ውሣኔ ከሰጠ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ እንዲቀጥል ማድረጉ የፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን የሚጥስና አስቀድሞ በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በድጋሜ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲወሰን የቀረበ ይሆናል። ቅጽ/10

ሰ/መ/ቁ.38745፡-የእስልምና ተከታይ የሆኑ ተጋቢዎች ጋብቻቸው እንዲፈርስ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ወይም ሁለቱም ከፈቀዱ ደግሞ ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት አስቀርበው እንደምርጫቸው ሊያፈርሱት ይችላሉ። በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሽማግሌዎች አፋትተውናል ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል ቀጥሎም የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ ሚስት የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል በደብዳቤ ገልያላታል የሚልን ክርክር ስልጣን የላቸውም በማለት መደበኛ ፍ/ቤት ቀደም ብሎ የሰጠውን የፍቺ ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ሚስት ከባል ጋር የነበራት ጋብቻ አልፈረሰም በማለት ሚስት ጋብቻዉን በመደበኛ ፍርድ ቤት አስፈርሰዉ እና ከጉባዔዉ ማስረጃ ይዘዉ ሌላ ስላገቡ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል በማለት የሚያስተላልፈዉ ቅጣት ትክክል አይደለም። ቅጽ/9

ሰ/መ/ቁ.220279፡-ባልና ሚስት በሸሪዓ ፍርድ ቤት የቤት ክርክር የሚያደርጉበትን ቤት ገዝቻለሁ በሚል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41 መሰረት አቤቱታ አቅርበው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በፍ/ቤቱ ከተፈቀደላቸው በኋላ የጣልቃገብነት ክርክር አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ የሸሪዓ ፍ/ቤት አቤቱታውን ተቀብሎ ከማከራከሩ እና ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን በተመለከተ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከላይ ከተጠቀሰው አዋጅ ድንጋጌ አንጻር ባልና ሚስቱ ከመኖሪያ ቤቱ ውጪ በሌሎች ንብረቶች ላይ የሚያደርጉትን የባልና ሚስት የንብረት ክርክር በማይነካ መልኩ ጣልቃ ገብ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸውን በቅድሚያ የማረጋገጥ በህግ ሀላፊነት የተጣለበት ያለበት በመሆኑ ጣልቃ ገብ የጣልቃገብነት ክርክር አቤቱታ ማቅረባቸውን በሸሪዓ ፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ እንደሆኑ በመውሰድ አቤቱታቸውን ተቀብሎ በዛው ፍ/ቤት አከራክሮ ቤቱን በተመለከተ እና ከቤቱ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ዉሳኔ ሊሰጥ አይገባም። ሰኔ 27/ 2014ዓ.ም

ሰ/መ/ቁ 201790፡- አንዱ በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ በሸሪዓ ፍርድ ቤት መታየት የጀመረ ጉዳይ በማንኛውም ምክንያት ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንደማይታይ እና በተመሳሳይ በመደበኛ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ጉዳይም ወደ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተዛውሮ የማይታይ መሆኑን የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቁጥር 188/1992 ቁጥር 5(4) ያስረዳል።

ወራሽነት፣ ሚስትነት እና ሞግዚትነት የተወሰነው በሃይማኖታዊው ፍርድ ቤት የሸርዓ ሕግን መሠረት አድርጎ ከሆነ ሃይማኖቱን መሠረት አድርጎ በሃይማኖታዊው ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሃይማኖታዊ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን መሰረት አድርጎ ውርሱን ማጣራት ያለበትም ማስረጃውን የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ነው። በሃማኖታዊ ሕግ

የተሰጠውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ መደበኛ ፍርድ ቤት ውርሱን ለማጣራት መሞከር ሃይማኖታዊውን ሕግ ከመደበኛ ሕግ ጋር መደባለቅ ከመሆኑም በላይ ክርክር በጀመረበት ፍርድ ቤት እልባት እንዲሰጠኝ የሚያደርግ እና መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ እንዳይገባ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 11(2) ያስቀመጠውን ክልከላን መተላለፍ ነው። የወራሽነት ማስረጃን መስረት የሚያደርገው የውርስ ማጣራት እና የድርሻ መለየት/ክፍፍል ተያያዥነት ያላቸው ክርክሮች እንጂ ምንም ግንኙነት የሌላቸው እራሳቸውን የቻሉ እና የተለያዩ ስላልሆኑ ክርክሩ የወራሽነት ማስረጃዉ በተሰጠበት ግራ ቀኙም ፈቃዳቸውን በሰጡበት የሸርዓ ፍርድ ቤት ፍፃሜ እንዲያገኝ መደረግ አለበት። መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ሰ/መ/ቁ.175719፡-ግራ ቀኙ ፈቃድ ሰጥተዉ በፍቺ ጉዳይ በሸሪዓ ፍ/ቤት እየተከራከሩ እያሉ እንደኖዉ ተከራከሪ ወገን ወይም ሁለቱም ይህ ክርክራቸዉ ወደ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተዘዋዉሮ የፍቺ ዉሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ለማቅረብም ሆነ የሸሪዓ ፍ/ቤቱ የፍቺ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል በሸሪዓ ፍ/ቤት ሳይሆን በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለማቅረብ አይችሉም። የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ የወሰነ ከሆነ፤ የፍቺ ዉጤቱንም ቢሆንም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ለመወሰን የሥረነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌደራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች እንጂ የፌደራል ፍ/ቤቶች አይደሉም። ስለሆነም ጋብቻቸዉን በተመለከተ የፍቺ ዉሳኔና ውጤቱ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥላቸዉ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ፤ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የግራ ቀኙ ጋብቻ እንዲፈርስ የፍቺ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ይኼዉ የሸሪዓ ፍ/ቤት ነዉ ::

በመሆኑም የፌደራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 5 እና 4 መሰረት ፈቃዳቸዉን እንደሰጡ የሚቆጠሩ ተከራካሪዎች በመካከላቸዉ የነበረዉ ጋብቻ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሰጠዉ የፍቺ ዉሳኔ ከፈረሰ፤ የፍቺ ዉጤቱንም ሰምቶ ለመወሰን የሥረነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ይኼዉ የሸሪዓ ፍ/ቤት በመሆኑ፤ የፌደራል ፍ/ቤቶች የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም ::ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም

ሰ/መ/ቁ.162194፡-የፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ለፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ቀርቦ የነጨረሻ ዉሳኔ ሳይሰጥበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ አይችልም። 29/8/2011 ዓ/ም